# **የዕውቅና ሽልማት ለዶ/ር አበራ ሞላ ተሰጠ**

ጋዜጣዊ መግለጫ



*“ዶ/**ር ኣበራ ሞላ** ፲ ፱፻ ፵ ዓ.ም ሸዋ ጠቅላይ ግዛት፣ ሰንዳፋ ከተማ የተወለዱ ኢትዮጵያዊ ናቸው። በ5 ዓመታቸው ትምህርት ጀምረው በ16 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨርሰዋል። ከ8 ዓመታት ኮሌጅ በኋላ በ25 ዓመታቸው የእንስሳት ሕክምና ዲግሪያቸውን ተቀበሉ። እ.ኤ.አ. በ1974 ከሠናይት ከተማ ጋር የጋብቻ ስነ ሥርዓት ከፈጸሙ በኋላ በ1975 በኮሎራዶ እስቴት ዩኒቨርሲቲ ለድሕረ-ዶክትሬት ዲግሪ ትምህርት ወደ ዩናይትድ እስቴትስ ኣምሩ። ኣመጣጣቸውም የኣሜሪካ መንግሥት የመጀመሪያን የእንስሳት ሓኪሞች ማሰልጠኛ ለኢትዮጵያ ማሠራት ስለወሰነ ነበር። በማካከሉ ኢትዮጵያ የኮምዩኒስት ጎራን ስለተቀላቀለች ባልና ሚስቱ ኣሜሪካ በመቆየት ወሰኑ። በኣሁኑ ጊዜ የሦስት ልጆችና ኣራት የልጅ ልጆች ኣሏቸው።*

*ዶክተሩ የኣበረከቷቸው የተለያዩ ቁምነገሮች ስለኣሉ የታወቁባቸውን በተሰጠኝ ጊዜ ማቅረብ ስለማይቻል ዋና ጉዳዮቹ የሚከተሉት ናቸው። ዶክተሩ የሚድንን ማ ስ በማስወገድ ከዓለም የእንስሳት ሓኪሞች ኣንዱ ታዋቂ ምሁር ናቸው። የግዕዝ ፊደል በኮምፒዩተርና የእጅ ስልክ ውስጥ በኣለውም ማጠቀም እንዲቻል የፈጠሩ ሊቅና የኣክሱም ሓውልት ከሮም ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ጣልያንን በማስፈራራት ወሳኙን እርምጃ የወሰዱ ኣርበኛ ናቸው።”*

ከእዚህ በላይ የቀረበውን የተናገሩት የኢትዮጵያ ቅርስና ውርስ ማሕበረሰብ በሰሜን ኣሜሪካ ፕሬዚደንት የሺጥላ ኣርኣያ ድርጅቱ ሰባተኛውን ዓመታዊ በዓል ህዳር ፲ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም ሲልቨር እስፕሪንግ ሜሪላንድ ሲያከብር ስለዶክተሩ የተናገሩት ነበር።

ዶ/ር ኣበራ ምንግግር ሲያኣደረጉ ከጠቀሷቸው ማካከል ግዕዝን በኣንድና ሁለት ሚገጮች ማከተብና ፊደሉን በእራሱ ፊደልና ገበታ ማጠቀም ስለተቻለ በሦስት ሚገጮች ማከተብ እንደሚያስፈልግ፣ የፊደል ሞክሼ እንደሌለው፣ ዓማርኛ ንግግር ውስጥ እንግሊዝኛ መቀላቀል ኣልኣስፈላጊነት፣ የብዙ ቊጥሮችን ኣጠቃቀምና ሰዋስው ማክበር ኣስፈላጊነት ይገኙበታል። ፊደላችን ድምጻዊ ስለሆነ የኦሮሚፉውንና የማንንም ድምጽ ሊወክል ስለሚቻል ሌላ ዓለም ልንሰውደው እንችላለን ብለዋል። ሕዝቡ ግዕዝ ኤዲትን ገዝቶ በተለያዩ ቋንቋዎቻችን ሚጻፍ ከኣልጀሚ ትውልዱ ወርቃማ ጊዜውን እያባከነና ሳይቸግረው ግዕዝን እያዳከመ መሆኑን ኣስጠንቅቀዋል። ሶፍትዌር የማ ዛ እንጂ የሚሰረቅ ኣይደለም ብለዋል።

ከእዚያም በዶ/ር ሞገስ ወልደሚርያም ኣስተዋዋቂነት *“የኢትዮጵያ የመሚር ባሕል እድሎቹና ችግሮቹ”* በሚል ርዕስ ንግግርና ውይይት በዶ/ር ኣክሊሉ ሃብቴ፣ ፕሮፌሰር ኣቻምየለህ ደበላ፣ ዶ/ር ኣበባ ፈቃደ እና ኣቶ ቴወድሮስ ኣበበ ቀርበው ዝግጅቱ በጥያቄና ሚልስ ተጠናቋል።

በዕለቱ ለተጋባዡ የቀረበው ጽሑፍ ውስጥ ስለ ዶክተሩ የተጻፈው የእንግሊዝኛ ጽሑፍ ትርጉም እንደሚከተለው ነበር።

*“ዶ/ር ኣበራ የግዕዝ ፊደል ኣባት የሚል ስም የተሰጣቸው ኣዳዲስ ነገሮችን የፈጠሩ ሳይንቲስት ናቸው። ከ፳፱ ዓመታት በፊት ግዕዝ በኮምፒዩተር እንዲከተብ ሲፈጥሩ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ የተወለዱትን የኢንጅነር ኣያና ብሩን የዓማርኛ የጽሕፈት ማኪና ፈጠራ በምሳሌነት*

*ተጠቅመዋል። ቢሆንም በላቲን ቀለሞች ምትክ የተሠሩት ቀርጥራጮች ትክክለኛ የዓማርኛ ፊደላት ስለኣልሆኑና ሚገጮዎቹ እንደፊደላቱ ብዙ ስለኣልነበሩ ለግዕዝ ፊደል የሚያስፈልጉትን ዶክተሩ ፈጥረዋል። ኮምፒዩተራይዝ የኣደረጉት ፊደላቸውም የዩኒኮድ ፊደል ሆኗል።*

*ከእዚሁ ጋር የተያያዘ በኮምፒዩተር ኣዳዲስ ኣከታተቦች፣ የፊደል ኣመዳደቦችና ገበታዎች ፈጥረዋል። ይህ ኢትዮጵያውያን ለመጀመሪያ ጊዜ በፊደላቸው በኮምፒዩተር እንዲጠቀሙ ኣስችሏል። እንዲህም ሆኖ ኢትዮጵያ ውስጥ የኣዕምሮኣዊ ፈጠራ ጥበቃ ሕግ በጊዜው ስለኣልነበረ የፈጠራቸውን መብት ኢትዮጵያ ውስጥ ማስጠበቅ ኣልቻሉም። ዋናው የዶክተሩ ዓላማም መብቱን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመጋራት ሁሉም ኣዕምሮኣዊ ፈጠራዎችን ማክበር እንዲጀምር ለማበረታታት ነበር።*

*በቅርቡም እያንዳንዱ የግዕዝ ቀለም ከሁለት ሚገጮዎች በኣልበለጡ ለማተብ ለኣስቻሉት ዘዴዎቻቸው የዩናይትድ እስቴትስና ኢትዮጵያ ማሜለከቻዎች ኣስገብተዋል። በዘዴዎቻቸውም ኢትዮጵያውያን በነፃ በዓማርኛ ኢንተርኔ ውስጥ እንዲጽፉና እንዲፈልጉ ኣበርክተዋል። በተጨማሪ ምዶ/ር ኣበራ በሰለጡኑበት የእንስሳት ሕክምንና ግዕዝን ኮምፒዩተራይዝ ሲያደርጉ የኣእምሮኣዊ የፈጠራ ባለቤትነት ተሰጥተዋቸዋል። ሲልቨር እስፕሪንግ ሜሪላንድ ሰባተኛውን ዓመታዊ በዓል ህዳር ፲ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም. የኣከበረው የኢትዮጵያ ቅርስና ውርስ ማሕበረሰብ በሰሜን ኣሜሪካ ዶክተሩን የበዓሉ የክብር እንግዳ ኣድርጓል።”*

ለዶክተሩ የተሰጠው የዕውቅና ሽልማት የዓማርኛ ትርጉም እንደሚከተለው ነው።

***“የኢትዮጵያ ቅርስና ውርስ ማሕበረሰብ በሰሜን ኣሜሪካ ለዶክተር ኣበራ ሞላ ዕውቅና በማስጠት ይኸንን ትልቅ ሽልማት የሚያበረክትላቸው በሠሩት በጣም ጠቃሚ ሥራ የግዕዝ የእስክሪንና የማተሚያ ፊደላት ስለፈጠሩ ነው። ይህ ፈጠራ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ቃላት ማተሚያ በመሆኑ የኢትዮጵያውያን ብሔራዊ ቋንቋ በሆነው ዓማርኛ ሕዝቡ በማሽ ባ በኮምፒዩተርና ተመሳሳይ መሣሪያዎች እንዲጠቀም ሆኗል። በተጨማሪም በሳይንቲስትነት፣ ተመራማሪነትና ሥራ ፈጣሪነት ለኣበረከቱት ዕውቅና የምንሰጠው በታላቅ ኩራት ነው።***

***የኣበረከትነው ምዕውቅና በማሕበረስቡ የዲሬክተሮች ቦርድና በሁሉም ኢትዮጵያውያን ስም ወሰን ከሌለው ምስጋና፣ ፍቅርና ኣድናቆት ጋር ነው።***

***በቦርዱ ዲሬክተሮች ወክልና ስም የሕብረተሰቡ ፕሬዚደንት፣ የሺጥላ ኣራኣያ።” ህዳር ፲ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም. November 19, 2017.***

ዶክተር ኣበራ ሞላ እና ባለቤታቸው ሠናይት ከተማ ከ፲ ፱፻ ፷፯ ዓ.ም. ጀምሮ የኮሎራዶ ነዋሪ ናቸው። የኢትዮጵያ ኮምፒዩተሮችና ሶፍትዌር ኩባንያ ባለቤቶችም ናቸው።

የዶክተሩ ኢ-ሜይል ኣድራሻ *geezedit@aol.com* ነው።